# የእናት እንባ

ኡኡታ በአራት ኪሎ    ኡኡታ በቦሌ
ኡኡታ በመረካቶ    ኡኡታ በጉለሌ
ጩኸት በቄራ    ጩኸት በጨርቆስ
ጩኸት በፒያሳ    ጪኸት በካዛንቺስ
ለቅሶ በኮልፌ    ለቅሶ በአልድ ኤየርፖረት
ለቅሶ በኮተቤ    ለቅሶ በላም በረት

ስትደክም ኖራ    ስትጥር ስትለፋ
አስተምራ አልብሳ    በምኞት በተስፋ
ራሷን እየራባት    ከአፏ ነጥላ አጉርሳ
በሃሳቧ እየታያት    ስትድረው ደግሳ

“ የሙሽራው እናት ውጪ ተከሰሻል
ይህን መሳይ ሎጋ ማን ውለጅ ብሎሻል
የዛሬ ዓመት የማሙሽ አባት
እንመጣለን ገና ለክርስትና ”

ተብሎ ተዘፍኖ    ተበልቶ ተጠጥቶ
ዘመድ ተደስቶ    እሷም ልቧ ረክቶ
ይህ ሁሉ ተስፋ    ይህ ሁሉ ምኞት
በአጭሩ ሲቀጭ    በወያኔ ጥይት
ዘመድ አዝማድ    የት ይደርሳል ያለው ወጣት
መንገድ ላይ ሲቀር    ከጫካ በወጣ አራዊት
ኡ ኡ አለች    እናት አለቀሰች

ኡ ኡ አለች    እናት ደረት መታች
ፊቷንም ቧጠጠች    ጨርቋን ሁሉ ጣለች
ያገር ያለህ አለች
ሕግ በሌለበት አገር    ፍትህን ለመነች

በካች አምና አምና    ከአምናም ዘንድሮ
ለልጇ እየተመኘች    የተሻለ ኑሮ
ደከመኝ ሰለቸኝ    መረረኝም ሳትል
ኑሮን ለማሸነፍ    ስትለፋ ስትጥር
ከሆዷ ቆጥባ    ለትምህርት ቤት ከፍላ
ልጇን አስተመራ    እራሷን በድላ
ቢከፋትም ስቃ    አይዞህ በርታ ብላ
ለእሱ አሚልታለት    ከራሷ አጉድላ
ደግሳ ድራ    የልጅ ልጅ ስማ
በኮልታፋ አንደበት    ተብላ እማማ

ኧረ ስንቱን አስባ ነበር     ስንቱንስ ዓልማ
ከንቱ ሆኖ ሲቀር     ይህ ሁሉ ድካሟ
በጠራራ ፀሐይ     ሲውጣት ጨለማ

ኡ ኡ አለች     እናት አለቀሰች
ኡ ኡ አለች     እናት ደረት መታች
ፊቷንም ቧጠጠች   ጨርቋን ሁሉ ጣለች
ያገር ያለህ አለች
ሕግ በሌለበት አገር   ፍትህን ለመነች

ጨኸቷ ባህር አቋርጦ     ልቤን ሲያናውጠው
ህዘኗ አጥንቴን ሰብሮ     መንፈሴን ሲያውከው
ንዴት ጠልቆኝ ገባ     እልህ አስጨነቀኝ
በቀልን አዝዬ     ቂምን አረገዝኩኝ
ትውልድ ይፍረድብኝ     ይህን ከረሳሁኝ
ፈጣሪዬ ይቅር አይበለኝ   ይህን ይቅር ካልኩኝ
ትውልድ ይፍረድብኝ     ይህን ከረሳሁኝ
ፈጣሪ ይቅር አይበለኝ     ይህን ይቅር ካልኩኝ

መስፍን ኃይሉ ብርሃኑ
ጥቅምት ፩፱፻፺፫ ዓ.ም.